# የሀገር ውስጥ ሕገ ወጥ የሕፃናት ዝውውር በኢትዮጵያ

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች:-**

ሰለሞን ወ/ተንሳይ

ህሊና መኮንን

- በማህበረሰቡና በፍትህ አካላት ባለሞያዎች ላይ ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ስራዎች መስራት አስፈላጊ ነው፡፡
- የወንጀሉ ተጠቂዎች ህፃናት በመሆናቸው ጉዳያቸው በፍትህ ስርዓት ውስጥ ማለፉ ብቻ በቂ ስለማይሆን ወደ ቤተሰባቸው (reunion) እና ወደ ማህበረሰቡ (ereintegration) የሚቀላቀሉበት ዝርዝር የሕግ ማዕቀፍ መቅረፅና ወደ ትግበራ መግባት አስፈላጊ ነው፡፡
- የወንጀሉ ባህሪ ከቦታ ቦታ እና ከክልል ክልል የሚደረግ በመሆኑ ወጥ የሆነ የአሰራርና የሕግ ማዕቀፍ በመዘርጋት በጉዳዩ ዙሪያ የሚሰሩ ባለሞያዎችም ሆነ ባለድርሻ አካላቱ በትብብር የሚሰሩበትን ሁኔታ ማጠናከር
- የወንጀሉ ሰለባዎች ሕፃናት በመሆናቸውና ወንጀሉም በህፃናቱ ላይ ከፍተኛ የስነልቦና እና ማህበረሰባዊ ቀውስ የሚያስከትል በመሆኑ ህፃናት በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ በሚያልፉበት ሂደትም ሆነ ከቤተሰብና ከማህበረሰቡ ጋር በማቀላቀል ሂደት የስነ ልቦና ባለሞያዎችንና የማህበረሰብ ሰራተኞችን በጉልህ ባሳተፈ መልኩ ማከናወን እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡
- በተለይ የመከላከል (prevention) ስራን መስራት እጅግ አስፈላጊ ነው ከዚህ ጋር በተያያዘ የወንጀል ቅጣቱን ማክበድ ብቻውን የሚፈለገውን ለውጥ ሊያመጣ አይችልም፡፡ ስለሆነም የማህበረሰቡንና በጉዳዩ ዙሪያ የሚሰሩ ባለሞያዎችን ንቃተ ህሊና ከማሳደግ ጎን ለጎን ህፃናቱ በሃገራቸው ላይ እምነት እንዲኖራቸውና በሃገራቸው ተምረውና ሰርተው የመለወጥ ራዕይ እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡
- ህፃናት በህግ በተቀመጠው መሰረት የስራ እድሜያቸው ከደረሰ ጀምሮ ሊሰሩ የሚችሏቸውን ስራዎችና ሊሰማሩባቸው የሚችላቸውን የስራ ዘርፎች በማስፋትና በማጠናከር በቂ የስራ እድል መፍጠር

- በህገ ወጥ የሕፃናት ዝውውርም ሆነ በህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ዙሪያ በሚመለከታቸው አካላት መረጃዎችን በአግባቡ በማደራጀትና በመያዝ ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት ፡፡
- አሁን በስራ ላይ ያለንን ህግ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት ከአለም አቀፍ ሕጎች ጋር ማጣጣም
- በህገ ወጥ የህፃናት ዝውውር ተጠቂ ህፃናትን በጊዜያዊነት ማቆየት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፖሊስ ጣቢያዎች የጊዜያዊ ማቆያ ቦታዎች የሚዘጋጁበት አሰራር ቢዘረጋና ይሄም በህግ ማዕቀፍ ውስጥ ቢካተት
- ወንጀሉ በህፃናት ላይ የሚያደርሰው ስነልቦናዊና አካላዊ ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ ወንጀሉ በተፈፀመ ጊዜ አጥፊዎችን ወደ ፍትህ ማምጣት ተጠቂ ህፃናትን ወደ ቤተሰብና ማህበረሰቡ የመቀላቀል ስራ እንዳለ ሆኖ በዋናነት ግን ባለድርሻ አካላት በተቀናጀ አሰራር ወንጀሉ እንዳይፈፀም መከላከል (prevention) ላይ ትኩረት አድርገው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡
- ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፉ የህፃናት መብት ኮንቬንሽንም ሆነ የህፃናት መብትን በሚመለተው የአፍሪካ ቻርተር በግልፅ እንደተቀመጠው የህፃናት የመጀመሪያ ትምህርት ግዴታ (child compulsory education) በኢትዮጵያ ህግ ማዕቀፍ ውስጥ ቢካተት ህፃናት ከቤተሰቦቻቸው የሚለዩባቸውን ሁኔታዎች ከመቀነሱም ባሻገር የወላጅ ግዴታዎችን በግልፅ በማስቀመጥ በኢትጵያ ያለውን ህገ ወጥ የሕፃናት ዝውውርን ከመከላከል አንፃር ጉልህ ሚና ይኖረዋል፡፡
- በአብዛኛው በሃገራችን በተለይ ሴት ህፃናት በህገ ወጥ መንገድ ከተዘዋወሩ በኋላ የሚዳረጉት ለቤት ውስጥ የጉልበት ብዝበዛ እንደመሆኑ የቤት ሰራተኞችን የስራ ሁኔታ የሚደነግግ የአሰሪና ሰራተኛ ህግ ማውጣት ህገ ወጥ የሃገር ውስጥ የህፃናት ዝውውር ወንጀልን ከመከላከል አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

- ለማንኛውም የሕፃናት መብቶች ለማስጠበቅ መሰረት የሆነው የልደት መዝገባ በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ የህፃናት መብት ጥበቃ ተግባራት ያጠናክራል፡፡
- ወንጀሉ እና ጉዳቱ ከፍተኛ በመሆኑና ባህሪው ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚቀያየር በመሆኑ በህገ ወጥ ህፃናት ዝውውር ዙሪያ (በሃገር ውስጥ የሚደረገውም ሆነ ከሃገር ሃገር በሚደረግ) በቂና ተከታታይ ጥናትና ምርምር በማድረግ የመፍትሔ ሃሳቦችን ማቅረብና ወደ ትግበራ መግባት
- የሕፃናት ውልደት ምዝገባ ህግ ቢወጣም በህጉ መሰረት በሃገሪቱ እስከ አሁን ተግባራዊ እየተደረገ ባለመሆኑ የሕፃናትን እድሜ በትክክል አውቆ ለህፃናቱ ተገቢውን መብትና ጥበቃ ለመስጠት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ፈጥሯል፡፡ ከህገ ወጥ የሕፃናት ዝውውር ጋር በተያያዘም ተጠቂ ሕፃናት በአብዛኛ የመጡበት አካባቢ በትክክል የማያውቁ በመሆናቸው ሕፃናቱን ወደ ቤተሰባቸው ለመቀላቀል አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ነገር ግን የሕፃናት ውልደት ምዝገባ ተግባራዊ ቢሆን ይሄን ችግር ሙሉ በሙሉ ያስቀረዋል፡፡
- ዝርዝር የሕፃናት ሕጎችን የያዘ የተጠቃለለ የሕፃናት ህግ (child Act) በማዘጋጀት ተበታትነው የሚገኙትን ሕጎች በአንድ ማጠቃለል፡፡ በዚህ ህጉ ለህግ ተርጓሚው እና ለሕግ አስፈጻሚው አካል ለአጠቃቀም ምቹ ማድረግ ፣ለህብረተሰብ እና የህጻናት ጉዳይ ይመለከተናል ለሚሉ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ተደራሽ ማድረግ ያስችላል፡፡